# የሰሞኑ የፖለቲካ ትርምስ- የመስመር ትግል ወይስ የስልጣን ሽኩቻ ?

## ወዴት እያመራን ነው ?

Aristotle: „ If each man follows his own individual will, the government of men’s lives is destroyed and totally dissolved.”

***<u>መግቢያ</u>***

የቅንጅት መሪዎች ከእስር ቤት ከተፈቱና ወደ አሜሪካ ከመጡ በኋላ በአንድ በኩል አቀባበሉና መስተንግዶው ጦፏል ፤ በሌላ በኩል ደግሞ አመራሩ ለሁለት ተክፍሏል በሚል በተለይም ይህንን ወይም ያኛውን ወገን እከተላለሁ በሚሉ ሁለት ኃይሎች መሀከል የማያስፈልግ ሽኩቻ ተፈጥሮ የፖለቲካውን አየር እያተራመሰው ነው። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የልዩነቱ መነሻ ሳይታወቅ በተለይም ውጭ አገር በሚገኙ ኢትዮጲያውያን መሀከል የሚሰነዘረው ቃል ፣ የሚወርደው ውርጂብኝ እጅግ የሚያስፈራ ነው። በ21ኛው ክፍለ ዘመን ጥቂቱ የሰው ልጅ በቴክኖሎጂ ተራቆ እኛ ሁሉ ተጠቃሚ በሆንበት ዘመን ለአንድ አፍታ እንኳ ቆም ብለን እራሳችንን መጠየቅ አቅቶን እንደዚህ ስንፋለጥ መስማቱ ፣ ዐይን ለዐይን ብንተያይ ወዴት መድረስ እንደምንችል መገመቱ ቀላል አይሆንም። በሰሞኑ ስድድባችን ከአንድ አገር የወጣንና ለዚያች አገር ብልጽግና ፣ ሰላም ፣ ለህዝቦቿ መፈቃቀርና በአንድ ላይ እጃችንን አጣምረን ለመስራት ታሪክ የጣለብንን ኃላፊነት ለመወጣት የምንችል አንመስልም። ብዙዎቻችን ለምን እንደምንታገል ገና ግልጽ የሆነልን አይመስለኝም። እጅግ የሚያሳዝን ድርጊት !!

የሰው ልጅ ከእንስሳ የሚለይባቸው ነገሮች ብዙ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ወደ አንዳች ፍርድ ወይም አድልዎ ከመድረስ በፊት የነገሮችን አመጣጥ ማውጣትና ማውረድ ብቻ ሳይሆን አንድ ጭፍን አቋም ቢወሰድ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ በቅጡ ማመዛዘን ያስፈልጋል። በተለይም ፊደል ቆጠርን ከሚሉ ሰዎች የሚጠበቀው ቁም ነገር አንድ ችግር ሲፈጠር ችግሩን ለማባባስ መሯሯጥ ሳይሆን ፣ በተቻለ መጠን የተቀጣጠለው እሳት ቶሎ ሊጠፋ የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር ነው።

በሰሞኑ ድርጊታችን የየካቲቱ አብዮት ከፈጠረው የማያስፈልግ ውዝግብና የህዝብ ዕልቂት በፍጹም የተማርን አይመስለኝም። በወቅቱ ጥቂት ለስልጣን የቋመጡ ግለሰቦች ተው እየተባሉ ባመረረ ጭንቅላታቸው እየተመሩ ለወጣቱና አገራችን በሁለትና በሶስት ትውልድ ልትተካቸው የማትችለውን ምሁራን እንድታጣ ተደርጋለች። በመሆኑም ዛሬ የምናያትን የተዋረደችና የተጎሳቆለች ኢትዮጵያን እንድንረከብ ተገደናል። እንደትላንትናው ዛሬም የሚሰራው ወንጀል በኛው ተማርን በምንልና ብልጽግናን እናመጣለን እያልን በምንመጻደቅ ምሁራን ነን ባዮች ነው። እስከዛሬ ድረስ በታሪካችን ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደተረጋገጠው በተራ ህዝብ ላይ የሚደርሰው ዕልቂት ሁሉ ተማርንና ተራቀቅን ብለው በሚመጻደቁ ሰዎች እንጂ ባልተማሩ ሰዎች አይደለም ።

ለመሆኑ የመማር ትርጉሙ ምንድ ነው ? ድሮ ትምህርት ቤት ስንሄድ የሚመስለን ፊደል ለመቁጠር ፣ መደመርና መቀነስ ለመማር ነበር። የመማር ዋናው ትርጉሙ ግን ይህ አይደለም። አውቆና ተመራምሮ ላልተማረው መልሶ በማስተማር አንድ ህዝብ የስልጣኔ ባለቤት ሊሆን የሚችልበትን መንገድ ለማሳየት ነው። የመማር ትርጉሙ ተንኮልን ቀስሞ አንዱን ከአንዱ እያምታቱና መጥፎ ነገር እየሸረቡ ሰም በማጥፋት በህዝቦች መሀከል አለመተማመን እንዲፈጠር ለማድረግ አይደለም። አንዱ ሌላውን እየጠለፈ ፣ አንዱ ከሌላው ለመብለጥ ሲል እሱን አጥፍቶ እራሱ ብቻ ሊኖር የሚችልባትን ዓለም ለመፍጠርም አይደለም። የመማር ትርጉሙ ውብ አገር ለመገንባት ሳይታክቱ መስራትና አንድ ህዝብ በሰላምና በመፈቃቀር ሊኖርባት የሚችልበትን አገር በመገንባት የታሪክን ኃላፊነት ተወጥቶ ለማለፍ ነው። የመማር ትርጉሙ ከዚህ ውጭ ሊሆን በፍጹም አይገባውም። አብዛኞቻችን ይህንን ወርቅ አስተሳሰብ ስተን በራሳችን ውስጣዊ ፍላጎት እየተመራን ወደ ማያስፈልግ ሽኩቻ እያመራን አገራችንን ወደ ሌላ የርስ በርስ ዕልቂትና ወደ ባሰ ድህነት እንዲሁም ደግሞ የውጭ ኃይሎች መናኮሪያ ልናደርጋት እየተዘጋጀን

ነው። አሁንም እየተመላለስን ለምን ተመሳሳይ ስህተት እንደምንሰራ ለመረዳትና ከዚህ የዙሪያ ጥምጥም ለመላቀቅ ይጠቅማሉ ብዬ በእኔ ግምት የማምንባቸውን አንዳንድ ሃሳቦች ለማስቀመጥ እወዳለሁ። የበሽታችንን ዋና ምክንያት እስካላወቅን ድረስ ለአገራችን የሚበጅ ስራ መስራት ስለማንችል፣ በዚህ ላይ ጠለቅ ያለ ውይይት ማድረጉ ጠቃሚ መስሎ ይታየኛል።

## የርዕየተ ዓለም ዝብርቅርቅነት ወይስ የህብረተሰብአዊ ንቃት-ህሊና ችግር !

አንዳንድ ሰዎች ከመሬት ተነስተው ለዲሞክራሲና ለነፃ ገበያ እታገላለሁ ሲሉ ግርም ይለኛል። አገራችንም የሚያስፈልጋት የሊበራል ዲሞክራሲ ስርዓት ነው እያሉ ለማሳመን ይሞክራሉ። ይህንን ሲሉ ግን የሚስቱት ሁለት ቁም ነገሮች አሉ። ይኸውም ሊበራል ዲሞክራሲና የነፃ ገበያ በምኞት የሚሆኑና ከላይ ወደ ታች ዝም ብለው የሚቀመጡ ነገሮች ሳይሆኑ የራሳቸው ታሪካዊ ሂደትና የዕድገት ደረጃ ያላቸው ከተወሰነ ህብረተ-ሰብአዊ ክንውን በኋላ ተግባራዊ ለሆኑ የሚችሉ መሰረተ ሀሳቦች ናቸው። ሁለተኛ፣ አንድ ሰው እነዚህን መሰረተ-ሃሳቦች ተግባራዊ አደርጋለሁ ብሎ ከመነሳቱ በፊት መጀመሪያውኑ የረጅም ጊዜ የጭንቅላት ስራ መስራት አለበት። ራሱን መልሶ መላልሶ መጠየቅ አለበት። የመጣበትን ህብረተ-ሰብ በቅጡ ማወቅ አለበት። ይህንን ለማድረግ ደግሞ በተወሰነ የአሰራር ስልት አንድን ህዝብ ወይም ሊከተሉኝ ይችላሉ ብሎ የሚገምታቸውን ሰዎች እየመላለሰ ማስተማር አለበት። ይህንን ሳያደርግ ግን ለዲሞክራሲ ሊታገል አይችልም።

ዛሬ የብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮችን የህብረተሰብ መዘበራረቅና የህዝቦችን መሰደድ እንዲሁም ደግሞ ለጦርነት ማገዶ መሆን ስንመለከት፣ በአንድ በኩል ምሁራዊ ፍላጎት በሌላ በኩል ደግሞ ህብረተሰብአዊ የማቴሪያል ተጨባጭ ሁኔታዎችና የህሊና አወቃቀሮች መሀከል አለመጣጣም ባለመኖሩ ምክንያት ነው። ብዙ ነገሮች ምኞት ይሆኑና ወደ ተግባር ይመንዘሩ በሚባልበት ጊዜ መደነባበርና መጠላለፍ ይመጣል። ለምንድነው አገራችንም ሆነ ብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች በቀላሉ ሊላቀቁ የማይችሉት የውስጥም ሆነ የውጭ አጣብቂኝ ውስጥ ወድቀው እዚያው በዚያው የሚማቅቁት ? ለምንድ ነው እነዚህ በምዕራቡ ዩኒቨርሲቲ ውሰጥ የተማሩት አንዳንድ የሚሊታሪና የሲቪል ቢሮክራቶችና የገዢ መደቦች ህዝቦቻቸው የሚመኟቸውን የስልጣኔ ፋና የማያጎናጽፏቸው ? ለምንስ የጦር እራት ያደርጓቸዋል ? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ አንዳንድ የፍልስፍና መሰረተ ሀሳቦችን እያነሳን እንወያይ።

አንድ በአገራችን የተለመደ ያሰራርና የአጻጻፍ ስልት አለ። የአንድን ህብረተሰብ ዕድገት መኖርና መጠናከር ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለማየት አለመቻል። በሌላ አነጋገር የአንድ አገር ትርጉሙ ምንድን ነው ? የሰው ልጅስ ፍላጎትና አገሩን ለመገንባት ሊጫወት የሚችለው ሚና ምን መሆን አለበት ? የትኛውንስ ፍልስፍና መመሪያ ማድረግና የትኛውንስ መንግድ ይዞ መጓዝ አለበት የሚሉት ጥያቄዎች ተነስተው ሰፊ ውይይት ተደርጎባቸው አያውቁም ። የአንድ አገር ህዝብ ዕድል በጥቂት ምሁራን ተዋናይነት ብቻ ይወሰን ይመስል ለነሱ ሜዳው ተለቆ እንደፈለጉ እየፈነጩበት አንድ ህዝብ ሲተረማመስና መንገዱ ጨልሞበት ይታያል። በተለይም ደግሞ በፍልስፍና ላይ የተመሰረተ ጥልቅ ዕውቀት ባልተስፋፋበት እንደኛ ባለ አገር ህዝብን በቀላሉ አሳስቶ የጨለማው ዘመን ኢንዲራዘም ለማድረግ ይቻላል። ይህ ዐይነቱ መንገድ ሆን ተብሎ ለመጀመሪያውኑ የታለመ ሊሆን ባይችልም የተወሰኑ ግለሰቦች ይህንን የአሰራር ስልት ከለመዱና በሌላ አስተሳሰብ እንዲገቱ ካልተደረገ ሌላ መንገድ የሌለ እየመሰላቸው በዚያው ይገፋበታል። ህዝቦችም በድህነትና በድንቁርና እዚያው በዚያው እየተንደፋደፉ እንዲኖሩ ይገደዳሉ። በተለይም በአሁኑ የኤሌክትሮኒክስ ዘመንና የተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች በዳበሩበትና በተስፋፋበት ዘመን ለአብዛኛው ህዝብ ዕውነትን ከውሸት፣ ትክክለኛውን ከሀቀኛው ለመለየት ይሳናዋል። በአሁኑ ወቅት አንድን ህዝብ ለማደንቆርም ሆነ ለማሰልጠን ማስ ሚዲያ የሚጫወተው ሚና በቀላሉ የሚገመት አይደለም።

እንደዚህ ዐይነት መወናበድ እንዳይመጣ፣ አንድ ህዝብ የሀቁን መንገድ ከተሳሳተው ለይቶ እንዲያውቅ ምርምርና ራስን የመጠየቅ ዘዴ ከተጀመረ ወደ ሶስት ሺህ ዘመን ሆኖታል። በሶክራትስና ፕላቶ በአንድ ወገን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በሶፊስቶች መሀከል የተደረገው ውይይትና ክርክር የሚያመለክተው አንድ ህዝብ የትኛውን መንገድ ቢከተል ዕወነተኛ ነፃነትን ሊጎናፀፍ ይችላል የሚለውን መስመር ለማስያዝ የተደረገ ትግል ነው ።

የዕውቀትንም አመጣጥና መዳበር ስንመለከት በሁለቱ ተጻራሪ የፍልስፍና መስመሮች ላይ የተመሰረተ ነው ። የተለያዩ ርዕዮተ ዓለሞች ፣ የተለያዩ ዕምነቶችና ባህሎች ቢኖሩም ማንኛውም ህብረተሰብ የመኖር ፍላጎትና ትግል በነዚህ ሁለት የፍልስፍና አመለካከቶች ላይ የተገነባ ነው። ይሁንና በአሁኑ የምዕራቡ ስልጣኔ የበላይነት ዘመን ከዕውነተኛው የእነ ሶክራቶስና ፕላቶን ፍልስፍናና የስልጣኔ መንገድ ይልቅ ኤምፐሪሲዝም ወይም የሶፊስቶቹ የማጭበርበር መስመር የበላይነትን ተጎናጽፎ ህዝቦች ሲተራመሱና ሀቀኛውን ከተሳሳተው መንገድ መለየት አቅቶአቸው ፍዳቸውን ሲያዩ ይታያል።

የምዕራቡ ስልጣኔ እየተስፋፋና እየዳባረ ከመጣ በተለይም ከ19ኛው ክፍለ-ዘመን ወዲህ እንደኛ ባለውና በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገር ህዝቦች ፣ ብዙም የምሁር እንቅስቃሴ ባልታወቀበት ህብረተ-ሰብ ላይ የጣለው የርዕዮተ-ዓለም ፣ የኢኮኖሚ ፣ የባህል ፣ የሚሊታሪና የፖለቲካ ጫናና ውዥንብር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ብዙም ምርምርና ጥናት ሳይደረግባቸው የተወሰዱ ዕውቀቶች ዕውነተኛ ስልጣኔን ከማጎናፀፍ ይልቅ አዲስ የኃይል አሰላለፍ በመፍጠርና በማጠናከር በቢሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች የድህነትና የጦርነት ሰለባ ለማድረግ በቅተዋል። የመፍጠር ችሎታን ከማዳበር ይልቅ የገዢ መደቦች መሳሪያ በመሆን ዕውነተኛ ዕድገት እንዳይመጣ እንቅፋት ሆነዋል። በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የበላይነትን ከተቀዳጀ ወዲህ በአንድ በኩል ለራሱ የሚያገለግሉ የብሄርተኝነት ስሜት የሌላቸውን ግለሰቦችንና ቡድኖችን በመኮትኮትና በማደለብ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ህዝቦችን እዚህና እዚያ በሚካሄዱ ትናንሽ ጦርነቶች( small scale wars) ውሰጥ በመክተት እንዲተራመሱና የድህነቱ ዘመን እንዲራዘም ያላደረገውና የማያደርገው ጥረት ይህ ነው አይባልም። በአንዳንድ አገሮች ደግሞ ሁኔታዎች ከቁጥጥር ሲወጡበት በኮሙኒዝም ስም በማሳበብና ብዙ የዋህ ሰዎችን በማሳሳት ለአገራቸው ክብር ቆርጠው የተነሱ ብሄርተኞችን ለመበታተን የማያደርገው ተንኮል ይህ ነው አይባልም። የቺሌው ፕሬዚደንት አዬንዴ መገደል ፣ በብዙ የላቲን አሜሪካ አገሮች የተካሄዱት የመንግስት ግልበጣዎችና የተቋቋሙት የሚሊተሪ አገዛዞች ፣ በግሬናዳና በኒካራግዋ ህዝቦች ላይ የተካሄደው ተዘዋዋሪና ቀጥተኛ ወረራ ፣ ዛሬ በብዙ የላቲን አሜሪካ ከተሞች የተስፋፋው ሰዎችን አላላውስ ያለው የማጅራት መቺዎች ዘረፋ በቀጥታ ከዚህ ከአሜረካን ኢምፔሪያሊዝም መረን የለቀቀ ህብረተሰቦችን ለማዘበራረቅ ከተጠነሰሰ ሴራ ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው።በተጨማሪም ከአራት ዐመት ጀምሮ ሳዳም ሁሴንን ቦንብ ለመስራት እየተዘጋጀ ነው ፤ ለህዝብ ዕልቂት የሚሆን የባይሎጂካልና የኬሚካል የጦር መሳሪያዎች በመስራት ላይ ነው ወይም ለዚህ ብቃትነት አለው በማለት በውሸት ማስረጃ የዓለምን ህዝብ አወናብዶ የተካሄደው ወረራ ለስድስት መቶ ሺህ ህዝብ ዕልቂት ምክንያት ሆኗል። ዋናው ምክንያት ግን ኢራክን እንደ ህብረ-ብሄር መኖር እንዳትችልና ለሶስት እንድትከፈል በማቀድ ነበር። ይህም ሁኔታ እስራኤልን በአካባቢው ብቸኛዋ ኃያል መንግስት ሆና እንድትኖርና አካባቢውን ለመቆጣጠር እንዲያስችላት የተዘጋጀ የረጅም ጊዜ ዕቅድ ነው። ከዚህ በተረፈ የመስከረም አስራ አንዱን "የአሸባሪዎች ድርጊት" አስታኮ በአፍጋኒስታን ህዝብ ላይ በየቀኑ የሚፈጸመው አሰቃቂ ድርጊት የምዕራቡ ዓለም መሳሪያውን ምክንያት እየፈለገ እንዲሞክር አስችሎታል። በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች የሰፈኑት አምባገነን መንግስታትና እንደዚህ ዐይነቱ የምዕራቡ ዓለም ሴራ ፣ በተለይም አሜሪካን መንግስታቱን እስከአፍጢማቸው በማስታጠቅ የሚፈጽመው ግፍ ለብዙ የዋህና የምሁር ጥልቀት ለሌላቸው ፣ እንዲሁም ደግሞ አንድ ህብረተሰብ እንዴት እንደሚገነባና ህብረተሰብአዊ መረጋጋት እንዴት እንደሚመጣ የማይረዱና በጊዜያዊ ብልጭልጭ ነገሮች ለሚታለሉ ሰዎች በቀላሉ ግልጽ ሊሆን አይችልም። በሌላ በኩልም ይህ የዓለምን ሁኔታ በዚህ መልክ መመልከት ለአንዳንዶች የነገሮችን ተዛማጂነት ለማይገነዘቡ በአዲስ መልኩ ያገረሸ የግራዎች በሽታ መስሎ ሊታይ ይችላል። እንደዚህ ዐይነቱ ክስ በዚህም በዚያም መጣ የዓለም ፖለቲካ በዚህ መልክ ካልታየና ካልተተነተነ የብዙ ሶስተኛው ዓለም አገር ህዝቦች ዕጣ ዘለዓለማዊ ድህነትና ጦርነት እንደሚሆን አያጠራጥርም።

ወደ አገራችንም ስንመጣ የዛሬውን የፖለቲካ መተረማመስ ለመረዳት ከላይ ባጭሩም ቢሆን የቀረበውን ሀተታ በመመርኮዝ ነው። ብዙዎች በተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ ያላለፉና በተለይም ደግሞ ሳያወጡና ሳያወርዱ የሊበራል ዲሞክራሲን ባንዲራ ይዘው የሚያውለበልቡ የአገራችንን የሰላሳ ዐመት የፖለቲካ ትርምስ የሚመለከቱት የውጭው ኃይል በተለይም ደግሞ የአሜረካን ኢምፔሪያለዝም ከሚያደርገው ሴራ ነጥሎ በመተንተን ነው። በተለይም የአሜሪካን ፍቅር የሚያንገበግባቸውና አሜሪካን አገር እነሱ የሚረዱት ዲሞክራሲ ስለሰፈነ አሜሪካን ሁል ጊዜም ሰላምን የሚሻና ለአገራችንም ብልጽግናን የሚመኝና የሚያግዝ እንደሆነ ነው። ከላይ እንደተቀመጠው ይህ የተሳሳተ አመለካከት በአንድ በኩል ጠለቅ ካለ ዕውቀት ማነስ የመነጨ ሲሆን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ለራስ ጊዜያዊ ጥቅም በመታለል ከውጭ ኃይሎች ጋር በመዳበል የህዝቦችን ዕውነተኛ ነጻነት በእንጭጩ ለማስቀረት

በማሰብም ነው። ይህ የመጨረሻው ነጥብ በየካቲቱ አብዮት ዘመን ጎልቶ የታየ ሲሆን ከአስራ ሰባት ዓመት ጀምሮ የሚካሄደው ትግል ግን ኢትዮጵያን ነጻ ማውጣት የሚቻለው በግሎባላይዜሽንና በነጻ ገበያ አማካይነት ብቻ ነው የሚለው የየዋሆች የትግል ፈሊጥ ሆኖ ብዙ ሰዎችን አሳስቷል። በመሆኑም ነው በኢህአዴግ መጠናከር ፣ የበላይነትን መቀዳጀትና የነጻ ገበያን ፖሊሲ በአነ ዓለም ባንክና አይ ኤም ኤፍ አማካይነት ተግባር ማድረግ መሀከል ያለውን መተሳሰርና የአሜሪካንን የውስጥ ለውስጥ ሴራና ድጋፍ ነጥሎ ማየት ያልተቻለውና ወደ ተሳሳተ ሀተታ የተገባው። የሊበራል ዲሞክራሲን ርዕይ ተግባራዊ እናደርጋለን የሚሉ ሁሉ በአስራ ሰባት ዐመት ትግላቸው ስለ አገራችን የኢኮኖሚና የህብረተ-ሰብ መዘበራረቅ አንድም ቦታ ላይ አመርቂ ትንተና ለመስጠት ያልቻሉት ከዚህ የውስጡንና የውጭውን ኃይል ያልተቀደሰ ጋብቻ አጣምሮ ለማየት ካለመቻል የተነሳ ነው።

የዛሬ አስራ ሰባት ዓመት በአሜሪካኖችና በእንግሊዝ የእንባ ጠባቂነት ሌሎችን ለብሄራዊ ነፃነት እንታገላለን የሚሉትንና ብሄራዊ ርዕይ ያላቸውን ኢትዮጵያውያን ኃይሎች አግልሎ የብሄረሰቦች ትርምስ ያለበት አገዛዝ በአገራችን ምድር ሲተከል ዋና ዓላማው ጠቅላላው የኢትዮጵያ ህዝብ ብሄራዊ ርዕይ ኖሮት እጅ ለእጅ ተያይዞ አንዲት ፣ ዲሞክራሲያዊትና የጠነከረች ኢትዮጵያን ለመገንባት እንዳይችልና ህዝቦቿ ከአሜሪካን በሚሰጥ ፍርፋሪ እየተመጸወቱ እንዲኖሩ የተቀነባበረ ሴራ ነው። ለዚህም ደግሞ አንዳንድ ጭንቅላታቸው የተጣመመ ኢትዮጵያውያን መንገድ ጠራጊና አጋዠ በመሆን የዛሬው እጅግ አሳዛኝ ሁኔታ እንዲፈጠር ከፍተኛ አስተዋፅዎ አድርገዋል። ስለሆነም ብዙም የፖለቲካ ልምድ ፣ ሰፋና ጠለቅ ያለ የቲዎሪ ዕወቀት የሌላቸው ይህንን መሰሪህ አስተሳሰብና ተግባራዊ መሆን በፍጹም አልተመለከቱትም። ይህንን በአሜሪካኖች አቀነባባሪነትና በጠቅላላው በምዕራቡ ዓለም የተጣለብንን ተንኮል እኛ የነቃን ኃይሎች ስናመለክት ወይ ይፌዝብናል አሊያም የአክራሪዎች በሽታ ነው ተብሎ ይታለፋል። ዛሬም ቢሆን በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የተጫነው መረን የለቀቀ ጨቃኝ አገዛዝና የህዝባችን የስቃይ ኑሮ እየታያቸው ዐይናቸውን ጨፍነው ጭንቅላታቸውን ጋርደው ብሄረተኛ ነኝ ፣ አገራችንና ህዝቧን ነፃ ሊያወጣና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል የኢኮኖሚ ፖሊሲ መነደፍ አለበት ፣ መንገዱም እንደዚህ ነው ተብሎ ሽንጥን ገትሮ ለማስረዳት በሚሞከርበት ጊዜ እነዚህ ኮሙኒዝምን ሳያዩ ኩሙኒዝም የሚያንገሸግሻቸው ኃይሎች በምንም ከኮሙኒዝም ጋራ የማይጣጣመውን የዕኩልነት ፣ የተቀደሰና በሳይንስ የተፈተነ አስተሳሰባችንን በማራከስ ስማችንን ሲያጠፉ ይታያሉ። በዚህም ምክንያት በአለፈው አስራሰባት ዓመት የተደረገው የመረረ ትግል ከኢህአዴግ የከፋፍለህ አገዛዝና የድህነት ፈልፋይ ፖሊሲም ጋር ብቻ ሳይሆን ከእነዚህ በዕውን ዓላማቸው ምን እንደሆን ካልታወቀ ትልቅ ሰዎች መስለው ብዙ የዋህ ኢትዮጵያውያንን ከሚያሳስቱ አደገኛ ሰዎችም ጋር እንደነበር ዛሬ መታወቅ አለበት።

በሌላ ወገን ደግሞ የኢህአዴግ የተተራመሰና ፀረ-ህዝብና ፀረ-ዕድገት ትግል አስመርሮአቸው ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት ብዙም የቲዎሪ ግልጽነት ሳይኖራቸው የኢትየጵያዊነትን ባንዲራ እያውለበለቡ እዚህና እዚያ የተቋቋቋሙ ድርጅቶች ስር የተሰባሰቡ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ብሩሁን ቀን የሚጠባበቁ ኢትየጵያውያን አሉ። ከነዚህ ውሰጥ ዘጠና በመቶ የሚሆኑት ቀና አመለካከት ሲኖራቸው በየጊዜው በመሪዎች መሀከል በሚደረገው የስልጣን ስግብግብነትና እንዲያም ሲል የአጭበርባሪነት ፖለቲካ ግራ ገብቷቸው የመንፈስ ጭንቀት ውስጥ ወድቀው ትክክለኛውን መንገድ ለማግኘት ሲተራመሱ ይታያል። እነዚህን ንጹህ ግን ደግሞ ግራ የተጋቡ እህቶቻችንና ወንድሞቻችንን ለመጥለፍና አጋሮቸቻው ለማድረግ እዚህና እዚያ የሚቅበዘበዙ ፣ ዛሬ የአንዱን ስም አንስተው የሚያወድሱ ፣ እሱ ደግሞ ገሸሽ ሲል ወይም ሌላ አቋም ሲይዝ ስሙን የሚያጎድፉና ያልተባለውን ተባለ ብለው በየፓል ቶክ ውሰጥ የሰው ስም የሚያጠፉ አሳሳች ኃይሎች ጥቂት እንዳይደሉ ግልጽ መሆን አለበት። እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የኛ የዕውነተኛ ብሄረተኞችና በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ነፃ የኢኮኖሚ ዕድገት አራማጆች የትግል ስልት ማንንም ላለማደናበር የሚልና ሁሉኑም ለማግባባት በሚለው መሰረታዊ አስተሳሰብ ላይ የተመረኮዘ የተቀደሰ ዓላማ ላይ የተመሰረተ ነው። ይህ አቀራረባችን ግን ሌላ ትርጓሜ እየተሰጠው የዋሁና ሰፊው ኢትዮጵያዊ ኃይል እንዲበታተን የሚደረገው ሴራ እየተጧጧፈ መጥቷል። ይህ ዐይነቱ ተንኮል ማንን ሊጠቅም እንደሚችል ግራ የሚያጋባ ነገር ነው።

የዛሬ ሁለት ዐመት የኢትዮጵያ ህዝቦች ግልብጥ ብለው ሲወጡና በአገዛዙ ላይ ያላቸውን ጥላቻ ሲያሳዩና ይህንንም በምርጫው ሲያረጋግጡ የሁላችንም ምኞት በጋራ ረጋ ባለ መንፈስ ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያን ለመገንባት ይቻላል የሚለው መንፈስ በጭንቅላታችን እንደተቀረፀ የማይታበል ሀቅ ነው። በሌላ ወገን ደግሞ ይህ የህዝብ ድል በተለያዩ ምክንያቶችና የዓለምን ፖለቲካ ጠለቅ ብለው በማይመለከቱ አንዳንድ ድርጅቶችና ግለ

ሰቦች ሊኮላሽ እንደሚችልና የሰቆቃውም ዘመን እንደሚራዘም እኔም ሆነ ሌሎች ኢትዮጲያውያን የፖለቲካ ታዛቢዎችና ተንታኚዎች ጠቁመን እንደነበር የማይታበል ሀቅ ነው ። የሚሰማን አጣን እንጂ !! ይህንን ባለመስማትና እነ አሜሪካንን በመተማመን የተደረገው የየዋሆች ፖለቲካ ወደ መጨረሻ ላይ በራሱ በአሜሪካን ትዕዛዝ የቅንጅት መሪዎች እንዳሉ ወደ እስር ቤት እንዲወረወሩ ተደርጓል። ይህ የሆነበት ምክንያት ፣ መሪዎች እስር ቤት ሲወረወሩ ትግሉ ይኮላሻል ፤ ህዝቡም መሪ ያጣል በሚል ግምት ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆን የቅንጅት መሪዎች አንድም ቦታ ላይ ቆመው ይህንን የአሜሪካንና የግብረ አበሮቹን ሴራ ለማጤንና ሌላ የትግል ስትራቴጂ ሊቀየስ የሚችልበትን ሁኔታ ይወያዩ አይወያዩ በግልጽ የሚታወቅ ጉዳይ የለም። እስር ቤት ከመግባትም በፊት ሆነ እስር ቤት ከገቡ በኋላ ፓርላማ ወስጥ እንግባ አንግባ በሚሉትና በኢህአዴግ ላይ የለሰለሰ ወይም የጠነከረ ፖለቲካ እንከተል በሚሉት መሀከል ሽኩቻ እንዳለ ግልጽ ነበር። ለዚህም ነው የተጠራውና ሰፊው ህዝብ በጉጉት ይጠባበቅ የነበረው ሰላማዊ ሰልፍና የቤት ውስጥ አድማ ሊከሽፍ የቻለው። ይህንንም በሚመለከት ልዩነቱ እዚህ ውጭ አገር ድረስ ተዛምቶ እኛን ሲያነታርከን ሰንብቷል።

እስር ቤት ከመግባታቸውም በፊትም ሆነ እሰር ቤት ከገቡና ከወጡም በኋላ በአመራሩ መሀከል የታየውና የሚታየው ልዩነት በመሰረቱ የመስመር ወይም የርዕዮተ-ዓለም ትግል ሳይሆን የስትራቴጂ ትግል መሆኑ ግልጽ እየሆነ መጥቷል። በሌላ በኩልም ይህንን ልዩነት ተጠቅሞ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ቀደም ብሎ ቅንጅትን እንደከፋፈለው ሁሉ አሁንም የተቀሩትን ለመከፋፈል የማያደርገው ሴራ ይህ ነው አይባልም። በተለይም "አክራሪ" የሚባለው የእነ አቶ ኃይሉ ሻውል ወገንና በዚህም በዚያም የተሰባሰበው ብሄረተኛውን ኢትዮጵያዊ ኃይል መበታተንና መመታት አለበት። በአዣን ፕሮቦካተሮች አማካይነት በእነ አቶ ኃይሉ ሻውል ላይ የሚደረገው ዘመቻ በቀጥታ በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የተቀነባበረ ለመሆኑ የሚጠቁሙ ብዙ ምልክቶች አሉ። የእነ አቶ ኃይሉ ሻውል ክንፍ ይህ ገብቶት ሰፊ ውይይት ያድርግ አያድርግ ፣ የአሜሪካንን ሴራ ተገንዝቦ ቁርጥ ያለ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ነፃነት መልሶ ሊያጎናጽፍ የሚችል ፖለቲካ ያራምድ አያራምድ ከአሁኑ መተንበይ ያስቸግራል። ማለት የሚቻለው በደርጅቱ ውሰጥ ትልቅ ውዥንብርና የዓለምን ፖለቲካ በሳይንሳዊ መነጽር የመመልከቱ ችግር እንዳለ ግልጽ ነው። በሌላ ወገን ግን ለጊዜውም ቢሆን በአሜሪካ የሚታዘዘውና የሚደገፈው የእነ አቶ መለስ ጨካኝ አገዛዝ እስትንፋስ በማግኘት ላይ ሲሆን ፣ የተደናበረውን ኃይል ደግሞ በዚህም በዚያም ብሎ ለመጥለፍ እየተጣደፈ ነው። በዚህ በተተራመሰ ሁኔታ ውስጥ አሜሪካን የሚመኘው በእነ አቶ መለስ ዜናዊ ጥላ ስር "የብሄራዊ ዕርቅን" ያካተተ መንግስት እንዲቋቋም የውስጥ ለውስጥ ስራውን ይሰራል። ይህ ተግባራዊ ይሁን አይሁን ወይም ደግሞ እነ አቶ መለስ የተቃዋሚውን ኃይል መዘናጋትና እርስ በርስ መበጣበጥ ተገንዝበው ብሄራዊ እርቅ እናደርጋለን እያሉ ትግሉን ያኮላሹት እንደሆን ከአሁኑ መገመት ያዳግታል። ወደድንም ጠላንም ፣ ዛሬም ሆነ ነገ  በቅንጅት መሀከል ያለው ክፍፍል እየሰፋ እንደመሄድ አያጠራጥርም። ይህ የእኔ ምኞት ወይም በተንኮል ላይ የተመሰረተ "ከእኔ በስተቀር" ከሚለው እርኩስ አመለካከት የመነጨ ግምት ሳይሆን ፣ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ የፖለቲካ አወቃቀርና ታጋይ ነኝ የሚለው የንቃተ ህሊና ማነስ ውጤት ነው። ለነገሩማ በዚያች ድሀ አገር ለምን ለዝንተ-ዓለማችን የመስመርና የስልጣን ትግል ብቻ እያካሄደን እንኖራለን። የእኔም ሆነ የሌሎች አገር ወዳዶች ህልም መሆን ያለበት ከስልጣን ባሻገር በጋራ እጅ ለእጅ ተያይዞ መተጋልና ዕውነተኛ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ የህዝባችንን መንፈስ የሚያረጋጋ የኢኮኖሚ ዕድገት ማምጣት ነበር።

እንግዲህ በእዚህ እጅግ ግራ በተጋባ ሁኔታ ውስጥ የእኛ የዕውነተኛ ዲሞክራቶችና የብሄራዊ ኢኮኖሚ ግንባታ አራማጆችና ታጋዮች ስልት ግለ ሰቦችን እያነሱ መከትከት ሳይሆን ፣ ለነፃ አገር መመስረት ፣ ለብሄራዊ ኢኮኖሚ ግንባታና ለጠነከረችና ህዝቦቿ በመፈቃቀር ሊኖሩባት የሚችሉበትን ኢትዮጵያ እንዴት ነው ልንገነባ የምንችለው ብሎ ማሳየት ይሆናል። በዚህም ትግላችን በቅንጅትም ሆነ በህብረት ውስጥ ያሉ ቀና ታጋዮችንና እንዲሁም ደግሞ ሰፊ ዕውቀት እያላቸው ግን ደግሞ ተሰላችተው እዚህና እዚህ የሚኖሩ ለስልጣን የማይስገበገቡ ኃይሎች አንድ ላይ በመምጣት ሰፊ ውይይት ማድረግና አገራችንን ከጥፋት የሚያድን ስትራቴጂ መንደፍ ይሆናል። የአሜሪካኑና በጠቅላላው ዓለምን በነፃ ገበያ ስርና በግሎባላይዜሽን ስም እንደፈለግሁ ህዝቦችንና ዓለምን አሻለሁ ፣ ኑሮዋቸውን አዘበራርቀዋለሁ ብሎ የተነሳውን የምዕራቡን ፖለቲካ በጥብቅ መከታተልና እያጠኑ ወደ ውጭ አውጥቶ መታጋልና ማታገል ያስፈልጋል። የተደናበረውንና በቀላሉ የዓለምን ፖለቲካ የማይረዳውን ከአጭበርባሪውና በዚህም በዚያም ብሎ ስልጣን ላይ ቁጥጥ ብሎ የህዝባችንን የድህነት ዘመን ከሚያራዝመው ነጥሎ ማውጣት ያስልጋል። አሁንም ቢሆን የግለሰቦችን

ስም በደፈናው እየጠቀሱ ጭፍን ውንጀላ ማካሄድ ሳይሆን ጽሁፎቻቸውን እያገላበጡና እየተነተኑ ለህዝብ በማሳየት ሰፊው ህዝብ ሀቀኛውን የስልጣኔ መንገድ ከአጭበርባሪው የአሜሪካኑ መንገድ ለይቶ እንዲረዳው ማድረግ ያሰፈልጋል።

## <u>የተወሳሰቡ ችግሮችና ጥያቄዎች !! በቀላሉ ልንመልሳቸው የማንችላቸው !!</u>

በአገራችን ታሪክ ውስጥ ሰፋ ያለ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ደግሞ አገርን በአጠቃላይ ለመገንባት የሚያስችል ምሁራዊ እንቅስቃሴ ተካሄዶ አያውቅም። ቢነሳ እንኳ ጠለቅ ያለ ውውይት ሳይካሄድ ወዲያውኑ ደብዛው ይጠፋል። እስከማውቀው ድረስ የአገራችንን የዕድገት ጥያቄ አንስቶ ለመወያየት የቻለው በ60 ዎቹ ገኖ የታየው የተማሪው እንቅስቃሴ ብቻ ነው። ይህም ቢሆን ከማርክሲዝም አንፃር ብቻ በመሆኑና መሰረታዊ ከሆነ የፍልስፍናና አጠቃላይ ከሆነ የስልጣኔ መንገድ ተነጥሎ በመካሄዱ ሰፋ ያለ ውይይት እንዳይካሄድ በር ዘጋ። በዚያን ጊዜ የተማሪው እንቅስቃሴ ያነሳቸው ጥያቄዎች ፣ በተለይም እንደመሬት ለአራሹና የዲሞክራሲያዊ መብቶች መለቀቅ ጉዳይ እጅግ አስፈላጊና በህብረተሰብአችን ውስጥም የተወሰነ ንቃ-ተህሊና እንዳመጡ የማይታበል ሀቅ ነው። በጊዜው የተከሰተው የማያስፈልግ መገዳደልና ይህም ደግሞ በህብረተሰብአችን ውስጥ ያመጣው መመሰቃቀል ከፍተኛ በመሆኑ ሰፊው ህዝብ አብዮትና ሶሻሊዝምን ለለመስማት ፈለገ። በጊዜው ማርክሲስት ነኝ ይሉ የነበሩ ግለሰቦችና አንዳንድ ድርጅቶች ደግሞ አቋማቸውን እንዲለውጡ ተገደዱ። አብዛኛዎቹ ደግሞ እስከናካቴው ትግሉን ትተው ወጡ። ብቻውን የቀረው የወታደር አስተዳደር ከአንድ እርምጃ ወደ ሌላ በመሸጋገር ህብረተሰብአዊ መመሰቃቀል አመጣ።

እ.አ ከ1989 ዓ.ም ወዲህ በኮሙኒሰት ጎራ የተከሰተው መንኮታኮት በዓለም አቀፍ ደረጃ የኃይል አሰላለፍ ለውጥ አመጣ። ከ 1979 ዓ.ም ወዲህ የታየው የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ ለውጥና በካፒታሊሰት አገሮች የታየው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለውጥ ፣ ማለትም በመንግስት ከሚደገፍ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ይልቅ  በኒዎ ሊበራል ርዕዮተ ዓለም የሚደገፍ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የበላይነትን ሲይዝ ብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች ከዚህ የምዕራቡ ካፒታሊዝም ግፊት ሊወጡ አልቻሉም። ዓለም አቀፋዊ የንግድ እንቅስቃሴ የዕድገት ዋናው መሰረት ሆኖ እንዲታይ በመደረጉና በመሰበኩ በተለይም ከሰሃራ በታች ያሉ ብዙ የአፍሪቃ አገሮች በዓለም አቀፍ የገንዘብ ፈንድና በዓለም ባንክ አማካይነት የመዋቅር መስተካከያ የሚባለውንና ሙሉ በሙሉ በገበያ የኢኮኖሚ ፍልስፍናና በግለሰብአዊ ድርጊትና ፍላጎት ላይ የተመሰረተውን ፖሊሲ እንዲከተሉ ተገደዱ። ይህ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ምንም ዐይነት ፍልስፍና የሌለው ብቻ ሳይሆን እንደየአገሮች የምጣኔ ሀብት ይዘት ለስልጣኔም ተብሎ ያልተዘጋጀ በመሆኑ ህብረተሰብአዊ መዘበራረቅን አመጣ። አንድን ህብረተሰብ ወደ ፍጆታ አጠቃቀም እንዲያመራና እንደ እንስሳ እንዲታይ የሚያደርግ በመሆኑ የመጨረሻ መጨረሻም እንዲበላላ የሚያደርግ ሆነ። አገሮችም የየግለሰቦች ድምር ሆነው ስለታዩና ስለሚታዩ ይህም ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት እንዲኖረው ተደርጎ በመሰበኩ አገሮች ወደ ተራ የንግድ እንቅስቃሴ መድረክ ተለወጡ። ሁሉም የየራሱን ጥቅም አሳዳጅ ሆኖ ታየ። በሰለጠነ ባህል ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተደገፈ እንቅስቃሴ ፣ ግለሰብአዊ ጥቅምን ክህብረተሰቡ ጥቅም ጋር ሊያስተሳስር የሚችል አንድ አገር እንደ ህብረተሰብ የመገንባት ፍልስፍና ቦታ ሳይጣቸው ቀረ። የመንግስትም ሚና ህብረተሰቡን ከመጥቀም ይልቅ በእነ ዓለም ባንክና በእነ አይ ኤም ኤፍ መዳፍ ስር በመውደቁ ጥቂት ግለሰቦች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደረገ እንጂ አጠቃላይ የሆነ የሀብት ዕድገት ሊመጣ አልቻለም። ዛሬ እንደምናየው ድህነትና የባህል ውድቀት እንዲሁም ደግሞ የህብረተሰብ መዝረክረክ የዚህ የኢኮኖሚ ፍልስፍና ውጤቶች ናቸው ማለት ነው።

በአገራችን ውስጥ አብዮቱ ያስከተለው አሉታዊ ውጤትና ይህ ዓለም አቀፋዊ የርዕዮተ ዓለም ሽግሽግ ብዙ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን የሊበራል ዲሞክራሲንና የሶሻል ዲሞክራቶችን ፍልስፍና እንከተላለን እንዲሉ አስገደዳቸው። ሁሉም በአንድ ጊዜ የገበያ ኢኮኖሚ አራማጆች ሆኑ። ይኸኛውን ወይም ያኛውን ርዕዮተ ዓለም እንከተላለን እንዲሉ ተገደዱ። በተግባር ካልሆነ በስተቀር አብዛኛዎቹ በአገር ቤት ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ደርጅቶችም ሆነ ፓርቲዎች በስልጣን ላይ ካለው የኢህአዴግ አገዛዝ የሚለዩበትም አንዳችም ነጥብ አልነበረም። ይለዩ የነበረው በመሬት ጥያቄ ላይ ነበር። ኢህአዴግ የመሬቱን አዋጅ አጥብቆ ሲይዝ ፣ አብዛኛዎቹ ደርጅቶች ግን የመሬትን መሸጥ መለወጥ

ይደግፋ ነበር። እነዚህ የሶሻል ዲሞክራሲንና የሊበራል ዲሞክራሲን ርዕዮተ-ዓለም እናራምዳለን ብለው የተነሱት ድርጅቶችም ሆነ ግለሰቦች ለምን ይኸኛውን መንገድ ለመከተል እንደፈለጉ አንዳችም ቦታ ላይ በቲዎሪና በፍልስፍና በመደገፍ ሰፋ ያለ ትንተና ሲሰጡ አልታዩም። ይህንንም ሲያስተጋቡ አምነውበት ሳይሆን ነፋስ ወደ ነፈሰበት ዐይነት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚውለበለበውን የነፃ ገበያ ፍልስፍና አብሮ ለማውለብለብ ብቻ እንደነበር መገመቱ ከባድ አይሆንም።

እንደሚታወቀው በአውሮፓ ምድር የህብረተሰብአዊ እንስቃሴዎችና የርዕዮተ ዓለም አነሳስ የራሳቸው ሂደት አላቸው። የሊበራሊዝም እንቅስቃሴ ከ17ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ በመንግስት የተደገፈ የኢኮኖሚ ፖሊሲን እየተቃወመ የመጣ ሲሆን ፣ የተፀነሰው ግን በሆበስና በጆን ሎክ ነው። የዚህ ፍልስፍና አነሳስ የፕላቶንን ዓለም አቀፋዊና ውስጣዊ ይዘት ወይም ከጭንቅላት በሚፈልቀው ሃሳብ ላይ የተመረኮዘውን የፍልስፍና መሰረት አናግቶ የተወሰኑ መደቦችን በላይነት ለማስፈንና ለማረጋገጥ የተቀነባበረ ራሱን የቻለ ርዕዮተ ዓለም ነው። በሌላ ወገንም የሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም ብቅ ከማለቱ በፊት የመንገስትን ሚና ጎላ ብሎ የሚያሳይ በካቶሊክ ፍልስፍና ላይ የተመሰረተ የሰብአዊነት አመለካከት እንደነበረም ይታወቃል። ይህ ማለት በአውሮፓ የህብረተሰብ እንቅስቃሴ ውስጥ አንድ ርዕዮተ ዓለም ብቅ ሲልና ይህ ህብረተሰቡን ያናጋል ተብሎ ሲታመንበት ወይም ደግሞ የመንግሰትን ሚና አጉልቶ ያሳያል ተብሎ ሲታመን ፣ ሌላ አማራጭ ፍልስፍና ብቅ ይላል። በመሆኑም የማርክሲስት ርዕዮተ ዓለም የኢንዱስትሪ አብዮት ያመሰቃቀለው ርዕዮተ ዓለማዊ የህብረተሰብ ውጤት ሲሆን አጉልቶ የሚሳያውም የወዝ አደሩን ሚና ነው። ማርክሲዝም በተለያዩ አገሮች በልዩ ልዩ መልክ እየተተረጎመ ተግባራዊ እየሆነ በመምጣቱ ልክ እንደ ካፒታሊዝም ውስጣዊ ኃይል ኖሮት ህብረተሰብአዊ ዕድገትን ሊያመጣ አልቻለም። ይህ ማለት ግን ድህነትን አላስወገድም ፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ማምጣት አልቻለም ማለት አይደለም። አተረጓጎሙም እጅግ ወደ ኋላ በቀሩ አገሮች በመሆኑ የግለሰቦች ነፃነትንና ድርጊትን በማፈን ጭካኔ የተሞላበት አገዛዝንም አስፍኗል። ይህ ደግሞ የሚገርም ነገር አይደለም። ብዙዎች ይህንን አብዮት ያካሄዱ አገሮች የአውሮፓው ህብረተሰብ የተጓዘበትን የህብረተሰብ ነፃነት እንቅስቃሴና የግሪኩን ስልጣኔ መልሶ የመገንባት ሂደት ውስጥ በፍጹም አልተጓዙም። ስለዚህም ህብረተሰብአዊ ድርጊታቸው ከጭካኔ ጋር የግዴታ መያያዝ ቻለ። የሶሻል ዲሞክራሲ እንስቃሴ ከወዝ አደሩ እንቅስቃሴ ተገንጥሎ የወጣና ካፒታሊዝምን ህብርተሰብአዊ ባህርይ እንዲኖረው ለማድረግ የተዘጋጀና ይበልጥ በሰራተኛው የሙያ ማህብር ላይ የተመካ እንስቃሴ ነው። ከ 1950-1980 ዎቹ ድረስ የመንግስት ሚናን አጉልቶ ቢያሳይምና በመንግስት የተደገፈ ካፒታሊዝም ስር እንዲሰድ ቢደረግም ፣ የሶሻል ዲሞክራሲ እንቅስቃሴ የርዕዮተ ዓለም ሽግሽግ አድርጓል። የበለጠ የኒዎ ሊበራል ርዕዮተ ዓለም ፍልስፍናን ተግባራዊ በማድረግ ከሰራተኛው ማህበር ጋር እያጋጨው መጥቷል። በከበርቴው መደብ ላይ የሚደረገው የቀረጥ ቅነሳ ፣ በተዛዋዋሪ ቀረጥ ጭመራና ለህብረተሰቡ የሚወጣው ድጎማ መቀነስ እነዚህና ሌሎች የኢኮኖሚ መስተካካያ መሳሪያዎች በህብረተሰቦች ውስጥ የሀብት መሸጋሸግ እንዳመጡ የማይታበል ሀቅ ነው። ለዚህም የሶሻል ዲሞክራት ፓርቲዎች ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። የትናንትናው ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ እንቅስቃሴ የዛሬው ዐይነት አይደለም። የዛሬዎችን ሊበራል ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች ስንመለከት ደግሞ የመንግሰትን ሚና በኢኮኖሚው ውሰጥ እንዳለ ይቃወማሉ። ኢኮኖሚው እንዳለ ልቅ እንዲሆንና የየግለሰብ ድርጊት ጎላ ብሎ እንዲታይ ግፊት ያደርጋሉ። ለዚህም በከበርቴው ላይ የተጫነው ቀጥተኛ ቀረጥ አሁን ካለበት በጣም ዝቅ እንዲል ይወተውታሉ። ፍልስፍናቸውም አጠቃላይ ህብረተሰብአዊ ጥቅም በግለሰቦች ተሳትፎ ሊመጣ የሚችልና የዚህም ድምር ውጤት እንደሆነ ይናገራሉ። ይሁንና ስልጣን ላይ ቢወጡ እንኳ ይህንን ፖሊሲያቸውን ተግባራዊ ለማድረግ በፍጹም አይችሉም። የህብረተሰቡ ግፊት ከፍተኛ ስለሆነ ከተወሰኑ ፖሊሲዎች ተሻግረው ሊሄዱ አይችሉም። እነሱም ቢሆን የሚናገሩትንና ፕሮግራማቸው ላይ የሰፈረውን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል ያውቃሉ። ተግባራዊም ቢሆን ህብረተሰብአዊ መናጋት እንደሚመጣ ያውቃሉ። ያም ሆነ ይህ በክርስት ዲሞክራቶች ፣ በሶሻል ዲሞክራቶች ፣ በሊበራል ዲሞክራቶችና የግሪን ፓርቲ በሚባለው መሀከል በፖሊሲና በርዕዮተ ዓለም መቀራረብ እየታየ ነው። ሁሉም ኒዎ-ሊበራል እሆኑ በመምጣት ላይ ናቸው ማለት ይቻላል።

ወደ አገራችን ስንመጣና ከአቅማችን በላይ የሆነው ውስብስብ ጥያቄና የአገራችን የተደራረበ ችግር በዚህ ዐይነቱ የአውሮፓ ህብረተሰብ የኢኮኖሚክ ፖሊሲ ሊፈታ ይችላል ወይ ? ይህንንም ወይም ያኛውን ርዕዮተ ዓለም ፣ ወይም ደግሞ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እናራምዳለን የሚሉት ድርጅቶች በርግጥስ የከበርቴው ህብረተሰብ ውስጣዊ ህግና የሚንቀሳቀስበት መሰረት ገብቷቸዋል ወይ ? በሰፊው ተወያይተውበታል ወይ ? ጥቅሙንና ጉዳትን አመዛዝነዋል ወይ ? ወይስ ለይስሙላ አልኩ ለማለት ነው ወይ ይህንን ርዕዮተ

ዓለም እናራምዳለን የሚሉት ? ብዙዎቹ ኢትዮጵውያን ድርጅቶችና ደጋፊዎቻቸው አንድ ወጥመድ ውስጥ የገቡ ይመስለኛል። በዓለም አቀፍ ደረጃ በነፃ ገበያና በግሎባላይዜሽን ስም የሚካሄድውን ዘመቻና ህብረተሰብአዊ መዋከቦች ወይ ሊገነዘቡ አይችሉም ፤ አሊያም አይመለከተንም በማለት የጭፍናቸውን የሚጓዙ ናቸው ። ይህ ግልጽ እስካልሆነ ድረስ ደግሞ ዛሬ በየፓል ቶኩ የሚሰማወን መፋተግ በሚገባ መረዳት ያስቸግራል። ይህንን የርዕዮተ ዓለም ውዠንብር ስመለከት እኔም ሆንኩ ሌሎች ተቃዋሚ ኃይሎች ከአቅማችን በላይ የሆኑ መዓት ነገሮች አሉ። ህብረተሰብአችን የሚፈልገውንና የሚመኘውን ዕድገት የመመለሱ ጉዳይ በጣም ውስብስብ እየሆነ መጥቷል ማለት ነው።ዛሬ ያለው የነፃ ገበያ ፍልስፍናና የግሎባላይዜሽን የበላይነት ደግሞ በቀላሉ የሚያፈናፍኑ አይሆኑም። በሌላ በኩል ግን ሊያፈናፍኑ የሚችሉበት መንገድም አለ። ይኸውም በኛ ተቃዋሚ በምንባለው መሀከል ዕድገትን የሚመለከት አንድ ዐይነት ግልጽ ስምምነት ያለ እንደሆነ ብቻ ነው። ይህ ጉዳይ ግልጽ እስካልሆነልን ድረስ እጅና እግራችንን ተጠፍረን በውጭ ኃይሎች አክራሪና ለዘብተኛ ተብለን እየተፈረጀብን ስንወናበድ እንከርማለን። ዛሬ ዩክሬይን ውስጥ የሚታየው ዐይነት የምዕራቡ አፍቃሪና አላፍቃሪ እየተባልን የነሱ መጫወቻ ሆነን እንቀራለን። በዚህም የድህነቱ ዘመን እየተራዘመ በመሄድ አገራችንም እንደ ህብረተሰብ የመኖሯ ጉዳይ እጅግ አጠያያቂ እየሆነ ይመጣል ማለት ነው።

ከዚህ ስንነሳ የህብረሰብአችንን ችግርና የሚንቀሳቀስበትን ህግ እንዲሁም ደግሞ ለመገንባት የምንፈልገውን ህብረተሰብ በሚገባ ለማወቅ የግዴታ የጭንቅላት ስራ መስራት አለብን ማለት ነው። በቀላሉ በሊበራል ዲሞክራሲና በሶሻል ዲሞክራሲ ስም እያታለልን ልንኖር እንችልም። የፖለቲካና የምሁር እንቅስቃሴ ጥራት ሳይኖራቸው ምርጫ የተደረገባቸው ናይጀሪያና ኬንያ የወደቁበትን ሁኔታ በሚገባ መመልከቱ ያስፈልጋል። ወይስ የምንሻው እንደዚህ ዐይነቱን የማጅራች መቺዎች ህብረተሰብ ነው ? ስለዚህ በተለይም እዚህና እዚያ ውርውር የሚሉና የፖለቲካ ካድሬዎች የሚመስሉ ዛሬ የግንባር ሚናን የሚጫወቱት ግለሰቦች ሰፊውን ህዝብ ከማሳሳት እንዲቆጠቡ ያስፈልጋል። ፖለቲካ ትልቅ ኃላፊነትን የሚጠይቅ ነው። ስነ-ምግባርንና ሀቀኝነት ይጠይቃል። ግልጽነትን ይሻል። የብዙ ሚሊዮን ህዝቦች ፍላጎት ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበት ወይም ሊኮላሽ የሚችልበትና ህዝቦች ለዝንተ-ዐለም ፍዳቸውን እያዩ ሊኖሩ የሚችሉበት መሳሪያ እንደመሆኑ መጠን በፖለቲካ ትግል ውስጥ እንሳተፋለን የሚሉ ሁሉ እራሳቸውን መልሰው መላልሰው መጠየቅ አለባቸው። በመሆኑም ማንም ሰው እየተነሳ የካድሬዎች ዐይነት ፖለቲካ ሊጫወት አይገባውም። ይህ ማለት ግን ለአገራችን የምናደርገውን ትግል እናቁም ማለት ሳይሆን ፣ የምንመራበት ፍልስፍናና ጨኸታችን ትክክል ነው ብለን አንድ ቦታ ላይ ቆም ብለን መጠየቅ አለብን ለማለት ነው። የሰው ልጅ ደግሞ ለመጠየቅ የተፈጠረ ስለሆነ በዚህ ተፈጥሮ በሰጠን ፀጋ በመጠቀም ቀናውን መንገድ ለመያዝና ለመደማመጥ እንሞክር። በዚህም መንገድ ብቻ ትክክለኛውን መንገድ መያዝ ብቻ ሳይሆን የታሪክንም ኃላፊነት ለመወጣት እንችላለን።

## <u>ትግሉ በምን መልክ ሊቀጥል ይችላል ?</u>

በቅንጅት አመራር መሀከል ክፍፍል ተከስቷል ከተባለና ከፊሉ አመራር ወደ አሜሪካና አውሮፓ ለስራ ጉብኝት ከመጣ ወዲህ በተለይም ውጭ ባለው የቅንጅት ደጋፊና አባል መሀከል የነበረው መከፋፈል በከፍተኛ ደረጃ ጦፏል። ትዝ እስከሚለኝ ድረስ አፍዴን የሚባለው በቅንጀት ዓለም አቀፍ አመራር ይሁን በሌላ አነሻነት ከመቋቋሙ በፊት በሁሉም የቅንጅት ደጋፊዎች ዘንድም ሆነ በየሰላማዊ ሰልፉ በሚሳተፉት መሀከል ሙሉ የወንድማማችነትና የእህትማማችነት መንፈስ ሰፍኖ እንደነበር ግልጽ ነው። ሁሉም ለአንድ ዓላማና በአንድ መንፈስ የሚታገል ነበር የሚመስለው። የቅንጅት ዓለም አቀፍ በደንብ ያልተጠና ከሌሎች ተገንጣይ ቡድኖች ጋር በኢፔኤልኤፍ አስተናጋጅነት የተካሄደው አብሮ የመታገል ስብሰባና ወደ አንዳች "ትብብር" መሸጋገር ለክፍፍሉ መንስዔ እንደሆነና ወደ መካረር እንዳመራ የማይታበል ሀቅ ነው። በተጨማሪም የራሱ የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር አመሰራረት ላይ ብዙዎቹ ጥያቄ ያቀርቡ እንደነበረና ከእስር ቤትም የተወሰኑ ሰዎች አመራሩን ውሰዱ የሚል ጽሁፍ ሊመጣ እንደማይችል ጥርጣሪያቸውን ያመለክቱ ነበር። ሁለቱም ተደምረው በሁለት አካባቢ የተሰባሰቡ የቅንጅት ደጋፍ ኮሚቴ አማካይነት በየፓል ቶኩ የሃሳብ ልዩነቱ በጋለ መልክ ይንፀባረቅ ነበር። ይህንን የጦፈ ልዩነትና መቃቃር የውጭ አመራር ነኝ የሚለው አካል በፍጹም መስመር ሊያሲዝ አልቻለም። ሁኔታው በዚህ መልክ ግሎ በየፓል ቶኩ ሲንፀባረቅ ከርሞ በአሁኑ ወቅት አመራሩ ልዩነቱን ወደ ውጭ

በይፋ ካወጣ በኋላ ፍጥጫውና ምናልባትም ወደ ሌላ ሁኔታ ሊያመራ የሚችል አስጊ ጉዳይ ተፈጥሯል። ዲያስፖራና ከረንት አፌርስ የሚባሉት ፓል ቶክ ውስጥ ገብቶ በመሀከላቸው የሚሰነዘረውን መካሰስና ስድብ ለሰማ በአንዳንድ አክራሪ ኃይል የሚሰነዘረው አነጋገር እጅግ የሚያስፈራ ነው። ምንም ዴሞክራሲያዊ ባህርይ የሌላቸውና የአነጋገር ስልትና ባህል የሚጎድላቸው ናቸው። ሁሉም በየቤቱ ተደብቆ ማይክሮፎኑን ራሱ ላይ አድርጎ ስለሚናገር የሚሰማውን ስሜት ለአንዳች ሰከንድ እንኳ ሳያስብ ይናገራል። አንድ እህታችን ከአንዱ የፓል ቶክ ውስጥ እየጮኸች ፣ በነሱ መቃበር ላይ ነው ዲሞክራሲን እንገነባለን ትላለች። ወንድምና እህቶቿን አስጨርሳ ወይም ሲያልቁ ዝም ብላ አይታ ምን ዐይነት ዲሞክራሲ መገንባት እንደምትችል በፍጹም ሊገባኝ አይችልም። ለእህታችን ግልጽ ያልሆነላት ነገር ግድያንና ስቃይን ከአገራችን ምድር ለማስወገድ እንደምንታገልና ሰላምና ፍቅር የሰፈነባትን ኢትዮጵያን ለመመሰረት እስከዛሬ እንደምንሰቃይ አልገባትም። እንደዚህ ዐይነቱ መጯጯህ ፣ አክራሪነትና ድንፋታ በአብዮቱ ወቅት የተካሄደውን መተላለቅ ትዝ ያሰኘኛል። ሁሉም በየፊናው አንዱ ሌላውን ጨርሶ የሚፈልገውን ዲሞክራሲ እገነባለሁ ብሎ ትንሽ ከተራመደ በኋላ ለጊዜው አጋር በሆነው ላይ ደግሞ በፊናው የፍየል ወጠጤ ይዘምርበት ነበር። እንደዚህ እያለ ሄዶ መጨረሻ ላይ ደርግ ወይም ደግሞ ኢሰአፓ የሚባል ፍጡር ብቻውን ይቀራል። እዚያ ውስጥም መተማመን አልነበረም። መጨረሻ ላይም ደርግ የእሳት እራት ይሆናል። ይከስማል። ዛሬ የምናያትን ኢትዮጵያን ልንረከብ በቃን። ይህ ሁሉ ውጤት የአርቆ አለማሰብ ጉዳይ ነው። ከዚህ ባሻገር በውድ አባቶቻችንና አስተማሪዎቻችን ፣ ከማንም በላይ አገራችን ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር እንዲሰፈን ዕድሜ ልካቸውን ሲታገሉ እንደቆዩት እንደ ፕሮፌሰር መስፈን የመሳሰሉት ታላላቅ ሰዎች ላይ የሚሰነዘረው ስድብ ለጆሮ ይቀፋል። በውነቱ እንደዚህ የመሳሰሉትን አፈኞችና ጋጠ ወጦች አገራችን አፍርታለች ወይ ? ወይስ ከሌላ ፕላኔት የመጡ ናቸው የሚያስብልበተ ደረጃ ላይ ደርሰናል። እንኳን ይህንን ታላቅና አንጋፋ አገር ወዳድ ምሁር ቀርቶ ሌላውንም ቢሆን የሚያውቀውንና የተሰማውን ከአንዳንዶቹ በተለየ መልክ ስላቀረበ የስድብ ውርጅብኝ ልናወርድበት በፍጹም አይገባንም። በአንድ በኩል በእንደዚህ ዐይነት ታላቅ ምሁር ላይ ስድብ እያወረድን በሌላ ወገን ደግሞ ዲሞክራሲ እያልን እየጮህን ምን ዐይነት ስርዓት ለመገንባት እንደምንፈልግ ግራ የሚያጋባ ነገር ሆኗል። በዚህ ተግባራችንና ጩኸታችን ብዙ ምራቅ የዋጡና ለአገራቸው ለመታገል ቆርጠው የተነሱ እህቶቻችንና ወንድሞቻችንን እያገለልን ነው። እንደማየውና እንደምሰማው ከሆነ አብዛኛዎቻችሁ ለመስማት የምትፈልጉትን ብቻ እንዲወራላችሁ ነው የምትፈልጉት። ይህ ጭፍን አስተሳሰብ ከዲሞክራሲያዊ ስነ-ምግባር ጋር በፍጹም ሊጣጣም አይችልም። ዲሞክራሲያዊ ህይወት ሊያብብ የሚችለው የተለያዩ ሃሳቦች ሲጋጩ ብቻ ነው። ተፈጥሮ በቅራኔ ህግጋት እንደምትገዛ ሁሉ ተጻራሪ አስተሳሰቦች ሲፋጩ ብቻ ነው መጨረሻ ላይ አንድ ጤናማ ህብረተሰብ ሊመሰረት የሚችለው። ከዚህ ውጭ ዲሞክራሲያዊ ህይወትና ግንባታ በፍጹም ሊኖር አይችልም። በተጨማሪም እያንዳንዱ ሰው የፈለገውን አቋም ይዞ ሊታገል ይችላል። አንዱ የቅንጅት ደጋፊ ሌላው ደግሞ የሌላው ድርጅት ደጋፊ ሊሆን ይችላል። በአንድ ድርጅትም ውስጥ የሃሳብ ልዩነትና የመጨረሻ መጨረሻ ተለያይቶ የራስን ፓርቲ መመስረት የተለመደ ጉዳይ ነው። ችግሩ ግን የተወሰኑ ሰዎች ውስጥ ለውስጥ ሌላ ስራ ሲሰሩና በስተጅርባ ደግሞ እናዋጋለን ከሚሉት ጋር በጎን ሄደው ንግግር ሲያደርጉና ለትግሉ እንቅፋት ሲሆኑ ነው። የሚሰሩት ስራዎች ሁሉ ግልጽነት ሳይኖራቸው ሲቀር ነው። ግልጽነት ካለ የትላንትናው ተቃዋሚ ኃይል ሂዶ ከኢህአዴግ ጋር ሊሰራ ይችላል። መብቱ ነው። በሳይንሱና በጨዋው መንገድ የመታገሉ ጉዳይ ደግሞ የኛ ፈንታ ይሆናል ማለት ነው።

በመሰረቱ ዛሬ በቅንጅት አመራር ውስጥ ተነሳ የተባለው ልዩነት በፍጹም ወደ መበላላት ሊያመራን አይገባውም። አንዱ አንዱን ቢቃወምም ከህጂ እያልን ብንሰዳደብም የምናገኘው ጥቅም ሊኖር አይችልም። በሌላ በኩል በማያስፈልግ ወቅት በተለይም በአንድ አመራር ውስጥ ልዩነት ሲፈጠር ትግሉን እንደሚያዳክመው የማይታበል ሀቅ ነው። የኛ መጯጯህ ግን ሁኔታውን ያባብሰዋል እንጂ መፍትሄ ስለማይሆን የነገሮችን ሂደት በደንብ አጥንቶ ሁኔታው ጋብ ሊል የሚችልበትን መንገድ መፈለግ የምሁራን ተግባር ነው። ሆኖም ግን ልዩነቱ መሰረታዊ ከሆነ ሁሉም በየፊናው ተሰማርቶ በሠለጠነ መልክ መታገል መብቱ ነው። ከመጀመሪያውኑ ልዩነቶች መነሳት የለባቸውም ፤ ከተከሰቱም በኋላ ደግሞ ያነሳውን ድምጥማጡን እናጥፋው ማለት የዲሞክራሲውን መንገድ ያጨልመዋል። የልዩነቶች መከሰት በኛ ብቻ አልተጀመረም። በታሪክ ውስጥ በብዙ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ልዩነቶች እየተከሰቱ በተለያየ ስልት መልስ አግኝተዋል። በአሁኑ የሀይ ቴክ ዘመን ግን ልዩነቶቻችንን መልክ ልናስይዝ የምንችለው በፍጥጫ ሳይሆን በሰለጠነ ዘዴ ብቻ ነው። በሌላ አነጋገር ከስሜታዊነት ትግል ተላቀን ወደ ቁም ነገሩና ወደ ሳይንሳዊው የትግል ዘዴ መመለስ አለብን። ይህ ማለት ኢትዮጵያን በሚመለከቱ መሰረተ ሃሳቦች ላይ ሁሉ ፣ ከዲሞክራሲ አንስቶ እስከ መንግስት አወቃቀርና ብሄራዊ ነፃነትና እንዲሁም ደግሞ ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የሰከነ ውይይት ማካሄድ አለብን። ህብረተሰብን ለመገንባት የማይጠቅም አጉል ፍጥጫ

ዝም ብሎ የራስን ስሜት ለማርካት የሚደረግ መራወጥ ነው። ዕውነተኛ ሳይንሳዊ ትግል የሚፈልግ ሃሳቡን በወረቀት ላይ እያሰፈረ ከፓል ቶክ ውጭ ወጥቶ ዐይን ለዐይን እየተያየ መታገል አለበት።

ይህ ከሆነና በአንዳንድ አጋጣሚዎች ብሄራዊ እርቅና ሰላም ያስፈልጋል እየተባለ የሚወተወተው የቱን ያህል ተግባራዊ ሊሆን ይችላል ? በእርግጥስ በዛሬው የፖለቲካና የኢኮኖሚ አወቃቀር ብሄራዊ ዕርቅ ማድረግ ይቻላል ወይ ? እነ አቶ መለስ ይህንን ያህል ዐመት ሲወተወቱ ከርመው አሁን ለብሄራዊ ዕርቅ ድርድር ዝግጁ ይሆናሉ ወይ ? የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የሚጫወተውን የከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲ እንዴት እንመለከተዋለን ? እነ አቶ መለስስ እሺ ቢሉ ከአሜሪካን ቁጥጥር ውጭ የሆነ የዕርቅ ድርድር ማድረግ ይቻላል ወይ በልን ትንሽ እንወያይ ።

## <u>የብሄራዊ ዕርቅ በአሁኑ አገዛዝና በኢትዮጵያ ሁኔታ ይቻላል ወይ</u> ?

ከረጂም ጊዜ ጀምሮ በአገር ሽማግሌዎችና በታወቁ ምሁር ኢትዮጵያውያን ይወተወት የነበረውና እስካሁንም የቀጠለው ሙከራ በተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎችና በመንግሰት ዘንድ የብሄራዊ ዕርቅ ያስፈልጋል እየተባለ ነው። እኔም ሆነ ማንም ሰላምን የሚፈልግና ሳይረበሽ ስራውን እየሰራ ለመኖር የሚሻ ወድ ዜጋ ዘላለም እየተጣላን ፣ የጎሪጥ እየተያየንና እየተገዳደልን ከመኖር ይልቅ ተባብረን አገር እንገንባ ሲሉት እምቢ የሚል ያለ አይመስለኝም። በታሪክ ውስጥም አንዳንድ ለስልጣን ከቋመጡ ግለሰቦችና ቡድኖች በስተቀር ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ሰላምን የሚሻና በድህነት የማትጠራ ኢትዮጵያን ነው ለማየት የሚፈልገው። ለዚህም ነው ህዝቡ በጾምም ሆነ በጸሎት በአገራችን ምድር ሰላም እንዲሰፈን የሚጸልየውና እግዚአብሄርን የሚማጸነው። ሀቁ ይህ ከሆነ ሰላምንና ዕርቅን የማይሻው ኃይል ማን ነው ? ለምንስ ብሄራዊ ዕርቅን አይፈልግም ? ህብረተሰብአዊ ትርምስንና ድህነትን ብቻ ለምን ይሻል የሚሉትን ጥያቄዎች ጠለቅ ብለን እንመርምር።

የዛሬው አገዛዝ ከዚህ የጥፋትና የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካው እንዲላቀቅ ያልተጻፈና ያልቀረበ ሃሳብ የለም። የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ "በደህናው ዘመን" የአርባ ገጽ የሰላምና የዕርቅ ደብዳቤ ለአቶ መለሰ ዜናዊ ጽፎ አስተላልፏል። እንደዚሁም ሌሎች የዛሬው አደጋ የታያቸው ምሁራኖች በትህትና ደብዳቤ እየጻፉ ሰላምና ዕርቅ እንዲመጣ ያላደረጉት ጥረት ይህ ነው አይባልም። ከአገዛዙ የተሰጠው ምላሽ ግን በጥፋት ፖሊሲያችን እንገፋበታለን ፤ የኛ ፖሊሲ የድህነት ፖሊሲ ነው ፤ ለአገሪቱ የሚበጃት ይኸኛው መንገድ ብቻ ነው ፤ ብሎ በጭፍን ሲገፋበት ከርሟል። ቆርጦም ከተነሳ ሰንብቶ ውሏል። ሀቁ ይህ ከሆነ የብሄራዊ ዕርቅ ያስፈልጋል እየተባለ የሚወተወተው አደናጋሪ መፈክር ለምን አስፈለገ?

በታሪክ ውስጥ እንደታየው የተለያዩ አገር መሪዎችን ጥበብ የተሞላበትና የተረጋጋ ፖለቲካ እንዲያካሂዱ ያልተደረገ ጥረት አልነበረም። ለመጀመሪያ ጊዜ ዲዮኒሲዩስ I የተባለው የስይራኩሰ መሪ ፕላቶ የተስተካከለና ጥበብ የተሞላበት አመራር እንዲያካሂድ ያልሞከረው ጥረት አልነበረም። ዲዮኒሲዩስ በፕላቶን አርቆ አሳቢ ፖለቲካ አልተስማም። በቤተ መንገስት ውስጥ ያሉ በፕላቶን ጥበባዊ ቀራረብ ያልተስማሙ ቀናተኞች ያድሙና አፍነው ገበያ ላይ ሊሸጡት ሲወስዱት ገበያ ላይ ያየው ኣደኛው ገንዘብ ከፍሏቸው ያስለቅቀውና ወደ አቴን ይልከዋል። አቴን በመመለስ የራሱን የፍልስፍና አካዳሚ በመክፈት በፍልሰፍናና በተፈጥሮ ሳይንስ ላይ ምርምሩን ቀጠለበት። እንደዚህ ዐይነት የተጣመሙ መሪዎችን በቀላሉ ማሳመን እንደማይቻል የተረዳው ፕላቶ አዲስ በሱ ፍልስፍና የታነፀ ትውልድ ማፍራት አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ በመቶ የሚቆጠሩ ሊቆች በማፍራት ለአውሮፓው ስልጣኔ መነሻ የሆነውን ሳይንሳዊ ምርምር ጥሎ አለፈ። በአውሮፓ ውስጥ ከተካሄዱት አሰቃቂ ጦርነቶች ፣ ድህነትና ረሀብ እንዲሁም የወረርሽ በሽታ በኋላ በታወቁ ፈላስፋዎችና ተመራማሪዎች የተደረሰበት ምርምር የሰው ልጅ ጭንቅላት እጅግ አስቸጋሪና ለመጥፎም ሆነ ለጥሩ ነገር የተዘጋጀ በመሆኑ ወደ ቀናው መንገድ ለመመለስ በጥበብና በልዩ ልዩ ውብ ስራዎች ማነፅ ያስፈልጋል የሚል ነው። የኩዛኑስ ፣ የላይብኒዝ ፣ የሼክሽፔርና የሺለር ድራማ ስራዎችና ግጥሞች የሚያረጋግጡት ፣ የሰውን ልጅ ጭንቅላት አርቆ እንዲያስብና ከጥፋት ተቆጠቦ ታሪክን እንዲሰራ ለማድረግ የግዴታ ሜታፊዚክሳዊ የጭንቅላት ስራዎች መሰራት እንዳለባቸው ነው። እነዚህ መመሪያዎች ዛሬም የሚሰራባቸውና ጊዜያዊና ዘለዓለማዊ እነደሆኑ ማረጋገጥ ይቻላል። ይህም ሆኖ በተጣመመ

አስተሳሰብ የሚገፋና ሁል ጊዜ በሰው ልጅ ስቃይ እየተደሰቱ የሚኖሩ እንዳሉ ዛሬ በገሃድ የምናየው ነው። ዛሬ በዓለም ላይ የሚካሄዱት ጦርነቶች ሁሉና የሚሰሩት ቦንቦች በዚህ እነ ፕላቶን በቀደዱት ዕውቀት ሆኖም ግን ለጥሩ ነገር ማዋል ባቃታቸው መሪዎች ፣ ጀኔራሎችና የሲቪል ቤሮክራቶች ነው። ታላቁ አሜሪካም ቢያንስ ባለፉት ሃምሳ ዐመታት ህዝቡንና ዓለምን ፍዳ የሚያሳየው የተቀደሰውን መንገድ መከተል ባቃታቸው እንደ ቡሽና ቼኒ በመሳሰሉት መሪዎች አማካይነት ነው። እነዚህ የሰይጣን ልጆች( The Children of satan) እየተባሉ በአንዳንድ የአሜሪካን ደራሲዎች የተጻፈላቸው ለዓለም ሰላም መደፍረስ ምክንያት ሆነው ፍዳችንን እያሳዩን ነው።

ወደ አገራችን ስንመጣ እንደዚህ ባለው ፕላቶናዊ የስልጣኔ መንገድ ባንጓዝም የዛሬው አገዛዝ በጭንቅላቱ የቀረጸውና በምንም የማይለቀቀው መንፈስና ዓላማ አለ። ይኸውም ህዝባችንን እያመሱና ወጣቱን ለጦርነት እየማገዱ መኖር ነው። የዛሬው የእነ ቡሽ ጁኒየር የፀረ አሸባሪዎት ዓለም አቀፋዊ ትግል ደግሞ አመቺ ሁኔታ ፈጥሮለታል። አገራችንን በዚህ በማያልቅ የአሜሪካን ጦርነት ስትራቴጂ ውስጥ ከቶ በጎረቤት አገሮች ማስጠላትና ህዝባችን ዘለዓለሙን ፍዳውን እያየ እንዲኖር ማድረግ ነው ። ለብዙዎች የመንግስትን አመሰራረት ፣ የህብረተሰብን አወቃቀርና የዕድገትን ሂደትና ደረጃ እንዲሁም ደግሞ የስልጣኔን ትርጉም በደንብ ለማይረዱ ይህ ዐይነቱ አቀራረብ በጥላቻ ላይ ወይም በአንዳች ዐይነት የአክራሪነት ዕምነት ላይ የተመሰረተ ጭፍን አቀራረብ ነው ብለው ሊገምቱ ወይም ሊቀበሉ ይችሉ ይሆናል። ለኛ የነፃነትን አርማ ይዘን ለምንታገል የኢትዮጵያ ህዝብ ወገኖች ግን አንድ ሰው ሌላውን የማሰርና የመግደል እንዲሁም ኑሮውን የማጨለም መብት የለውም። እንዲሁም እያንዳንዱ ግለሰብ በእግዚአብሄር አምሳል የተፈጠረ እንደመሆኑ መጠን የመፍጠር ችሎታውን እየተጠቀመ ኑሮውን አሻሽሎ በጋራ የተከበረች አገር የመመስረቱ ጉዳይ የተፈጥሮ ህግ ነው። ይህንን ማድረግ የማይችል ህዝብ ከእንስሳ የማይሻልና ኑሮዉ ሁሉ ስቃይ የተሞላበትና መሰደድ ይሆናል። ስለሆነም በአንድ አገር የተወለደና የሚኖር ህዝብ በማንም ሳይጨቆን ጤናማ አገር መገንባት አለበት። አንድን አገር የመገንባት ጉዳይ የጥቂት ሰዎች መብትና ኃላፊነት ብቻ አይደለም። የጠቅላላው ህዝብ መብትና ፍላጎት ነው። በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የሚኖረውም አገዛዝ አንድን ህዝብ እንደ ከብት መንዳትና ሀብቱን ለውጭ ከበርቴዎች መቸብቸብ ሳይሆን የስልጣኔውን ፈለግ ማሳየትና ህዝብን አስተባብሮ የጠነከረች አገር መገንባት ነው። በስልጣን ያሉ የገዢ መደቦች ልዩ ፍጡሮች አይደሉም። ወይም ደግሞ አንድን አገር አስተዳድሩ ወይም እንደፈለጋችሁ ጨፍሩበት ብሎ እግዚአብሄር የላካቸው አይደሉም። ሰው ሁሉ ሰው ነው። አንዱ ከሌላው ሊበልጥ አይችልም። ይህንን መሰረታዊ የተፈጥሮ ህግና የሰውን ልጅ መብት የሚስት ወይም ደግሞ ራሱን ከሌሎች ከፍ አድርጎ የሚመለከት ጭንቅላቱ ትክክል አይደለም ብለን ነው የምናምነው። ትክክለኛውም መንገድ ይህ እህትማማችንና ወንደማዊ ፍቅርን የሚያረጋግጠው የስልጣኔ ፈለግ ብቻ ነው መረጋጋትንና ሰላምን ሊያመጣ ይችላል ብለን አምነን የተቀበልነው።

ከዚህ መሰረታዊ ሀቅ ስንነሳ የዛሬው አገዛዝና ህዛባችን ሁለት የተለያዩ ፍጡሮች የሆኑበት ደረጃ ውስጥ ነው የምንገኘው። አገዛዙ ልዩ ፍጡር ፣ ህዝባችን ደግሞ እንደ አልባሌ የሚታይና በአገሩ ላይ ምንም መብት የሌለው የሆነበት ነው። ሌሎች የዲሞክራሲ ዝባዝንኬዎችን ትተን የፈለገው አገዛዝ ቢሆን በአጋጣሚ የያዘውን ስልጣን ተጠቅሞ አንድን ህዝብ እንዳሻው የማሰቃየት መብት የለውም። በየትኛውም ፍልስፍናና ህግም አልተጻፈም። ከዚህ እጅግ ቀላል ነገር ግን ደግሞ መሰረታዊ ሀቅ ስንነሳ የኢትዮጵያ ህዝብ አገዛዙን ዕርቅ የሚጠይቅበት ምንም ምክንያት የለም። ወይም ደግሞ ብሄራዊ ዕርቅ ያስፈልጋል እተባለ ውትወታ እየተደረገ ህዝብን ማዘናጋትና የጨለማውን ዘመን ማራዘም አስፈላጊ አይደለም። ዕርቅ ያስፈልጋል ከተባለ በዳዩ ነው ተነስቶ እስካሁን ድረስ ወንጀል ስለሰራሁ ከእንግዲህ ወዲያ እንደማንኛውም ዜጋ በሰላም መኖር ስለምፈልግ ይቅርታ ይደረግልኝ ብሎ የኢትዮጵያ ህዝብ እግር ስር መውደቅ ያለበት።

ጉዳዩ እንደዚህ ግልጽ ከሆነ የብሄራዊ ዕርቅ ያስፈልጋል እያሉ የሚወተውቱ የአገር ሽማግሌዎችና አንዳንድ ምሁራን መጠየቅ ያለባቸው አንድ አገዛዝ አንድን ህዝብ እንደዚህ ረግጦ የመግዛት መብት አለው ወይ ብለው ነው ? እንደምገምተው ከሆነ እነዚህ ሰዎች ስለሰው ልጅ መብትና እኩልነት የተሳሳተ አመለካከት ያላቸው ነው የሚመስለኝ። መብት ለጥቂት ሰዎች ብቻ ተባርኮ የተሰጠና የገዢ መደቦች በአስፈለጋቸው ጊዜ እየቆጠቡና እየለኩ የሚሰጡት ነገር አድርገው የተገነዘቡ ይመስለኛል። ይህንን የፍልስፍና ጥያቄ ትተን ወደ ተጨባጩ ሁኔታ ስንመጣ በዛሬው ወቅት ብሄራዊ ዕርቅ ሊመጣ የማይችልባቸው አያሌ ምክንያቶች አሉ። አገዛዙ ህዝቡን ረግጦ ለመግዛት ይችል ዘንድ በአፋኙ ሲአይ ኤ እየታገዘ እስከአፍጢሙ የታጠቀ የስለላ ኃይል ዘርግቷል። ህዝባችን በፍርሀት ተውጦ

የሚኖር ፣ ጠዋት ወጥቶ ማታ ተመልሶ ይግባ አይግባ በእርግጠኝነት የሚሰማው አይደለም። በዚህ ላይ ባስፈለገው ጊዜ ሊንቀሳቀስ የሚችልና ህዝቡን ሊጨፈጭፍ የሚችል አረመኔያዊ ኃይል ተዘጋጅቶ ይገኛል። የሰኔው አንድ ጭፍጨፋ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። ከዚህ በተረፈ መንግስትና አገዛዝ የተጣመሩበት ፣ በህግ አውጪውና አስፈጻሚው መሀከል ምንም ልዩነት የሌለበትና ፍርድ ቤቱ ነጻ ያልሆነ ወይም ፖለቲካዊ ቁጥጥር ያለበት ነው። በተጨማሪ በመንግስታዊ ኢንስቲቱሽኖች ውስጥ የውጭ አገር ዜጎች ተሰግስገው አገሪቱን ወደ ቅኝ አገዛዝ እየቀየሩ ነው። በዚህ እጅግ በተሰበጣጠረ ሁኔታ ውስጥ እንዴት አድርጎ ብሄራዊ ዕርቅ ማድረግ እንደሚቻል እዚህና እዚያ የሚረረጡት ሽማግሌዎችና አንዳንድ ምሁራን ቢያስረዱን ደስ ይለናል።

ከዚህ አጅግ አስጀጋሪ ሁኔታ ወጥተን ወደ ኢኮኖሚው ስንገባ የአገሪቱ መሰረታዊ የኢኮኖሚ አውታሮች በመንግሰትና በአላሙዲን ቁጥጥር ስር የወደቁና ለነፃ ውድድር መፈናፈኛ የማይሰጡ ናቸው። ባለስልጣናቱ የመንግስቱን መኪና ተገን አድርገው ሀብት አካብተውና ከውጭው ኃይል ጋር በመመሰጣጠር ሀብት በአንድ በኩል ወደ ውስጥ ሰፋ ባለ የኢኮኖሚ መሰርት ላይ እንዳይዘረጋ እንቅፋት ሆነዋል ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የማይሆን ፖሊሲ በመከተል ወደ ውጭ እንዲፈስ እየተደረገ ነው። ለዚህ ደግሞ አገዛዙ በአሜሪካን አዛዥነት የተከተለውና የሚከተለው የኒዎ ሊበራል ወይም የቀኞች የኢኮኖሚ ፖሊሲ ጥቂቱን ሀብት እየዘረፈ ሀብታም ሲያደርግ ፣ አብዛኛውን ህዝብ ደግሞ ወደ ለማኝነትና ወደ ድህነት ገፍትሮታል። የዛሬው አገዛዝ ትክክለኛው የዕድገት ፈለግ ይህ ነው እያለና ኢኮኖሚው ይህን ያህል በመቶ አድጓል እያለ በህዝብ ላይ እየቀለደ የሚኖር ሆኗል። ከዚህ ስንነሳ በኛና በአገዛዙ መሀከል በመንግስት ፍልስፍናም ሆነ በኢኮኖሚ ፖሊሰው መሀከል የሰማይና የመሬትን ያህል ርቀት አለ።

ባጭሩ እኛ አገር ወዳዶችና ዴሞክራቶች ህዝባችን የማይፈራበት ነፃ አገር ይመስረት ስንል ፣ አገዛዙ የለም ይህ ሊሆን በፍጹም አይችልም ይለናል። አገራችን ብሄራዊ ነጻነቷ መከበር አለበት ስንል ፣ አገዛዙ በዘመነ ግሎባላይዜሽን ብሄራዊ ነጻነት ብሎ ነገር የለም ፤ ስለዚህም ኢትዮጵያ የማንም የውጭ ኃይል መፈንጫና ከዚያ እየተነሳ ሌሎች አገሮችን የሚወረርባት አገር ናት ይለናል። ስለዚህም ይለናል ፣ ጥንት መሪዎቻችን ሁለት ጋሻ መሬት የሚያህል ለኤምባሲዎች መስሪያ እንደሰጡ ሁሉ እኛ ደግሞ በበኩላችን አሜሪካን ትልቅ ህንፃ የሚሰራበትንና የሚሊተሪ ኮማንድ የሚያቋቋምበትን ለክተን በመስጠት ከዚህ እየተነሳ አፍሪቃን ሁሉ እንዲያስስ እናደርጋለን ይለናል። እኛ ህዝቡ ሃሳቡን በነጻ የሚገልጽበት መድረክ ያስፈልጋል ስንል ፣ ከኔና እኔን ከሚደግፉ በስተቀር ሌላው ሃሳቡን መግለጽና ማንሸራሸር የለበትም ይለናል። እኛ ለህዝባችን በሳይንስን በቴክኖሎጂ ላይ የሚንቀሳቀስ ኢኮኖሚ መገንባት አለበት ስንል ፣ አገዛዙ ኢትዮጵያ ለልመና የተፈጠረች ስለሆነች ሳይንስና ቴክኖሎጂ አያስፈልጋትም ይለናል። እኛ ለአንድ አገር የውስጥ ገበያ መዳበርና መስፋፋት የግዴታ ውብና የተወሳሰቡ ከተማዎች መገንባት አለባቸው ስንል ፣ የለም የኢትዮጵያ ህዝብ መኖር የለመደው በመንደርና በጎጆ ውስጥ ነው ይለናል። እኛ ሰፊው ህዝብ ከዚህ ከተጨማደደ ኑሮ ተላቆ በንጹህ ቤቶች መኖር አለበት ስንልና ለዚህም የአጭርና የረጅም ጊዜ የከተማ ግንባታ ዕቅድ ይውጣ ስንል ፣ ይህ በፍጹም ሊሆን የሚችል ነገር አይደለም ይለናል። እኛ ጠንካራና በቴክኖሎጂና በሳይንስ ላይ ያተኮረ ሰፋ ያለ የብሄራዊ ከበርቴ መደብ ያስፈልገናል ስንል ፣ አገዛዙ የለም የነጋዴና ቶሎ ቶሎ ሀብት እያካበተ የሚኖር መደብ ነው የሚያሰፍልገን ይለናል። እኛ የአገሪቱ ገበያ የግዴታ ከውጭ በሚመጣ ዕቃ መዳከም የለበትም ስንል ፣ አገዛዙ የለም ዓለም አቀፋዊ የንግድ ፍልስፍና ይህንን አይፈቅድም ይለናል። እኛ ጠንካራና በልዩ ልዩ ባህል ነክ ነገሮች የዳበረ ህብረተሰብ ያሰፈልጋል ስንል ፣ አገዛዝ የለም የተዝረከረክና የዓለም ማህበረሰብ የሚሳለቅበት ህብረተሰብ ነው የሚያስፈልግ ብሎ ያፌዝብናል። ባጭሩ በኛ አገር ወዳዶችና ዲሞክራቶች እንዲሁም ደግሞ በሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድ ወገንና በሌላ ወገን ደግሞ በዛሬው በአሜሪካን በሚደገፈው የኢህአዴግ አገዛዝ መሀከል የሰማይና የመሬትን ያህል ርቀት አለ። የኛው መንገድ የስልጣኔና የህብረሰተብአዊ ስምምነት ሲሆን ፣ የወያኔው ደግሞ የጥፋትና የጨለማ ነው። በዚህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ እንዴት አድርጎ ብሄራዊ ዕርቅ ሊመጣና እንዴትስ መደራደር ይቻላል። ይህ ግልጽ እንዲሆንልን ሽማግሌዎችን በአክብሮት እንጠያቃቸዋለን።

ከዚህ ግልጽ ግን ደግሞ አስቸጋሪ ከሆነ ሁኔታ ስንነሳ ምን ዐይነት የትግል ስትራቴጂ መቀየስ አለብን የሚለውን ጥያቄ እያነሳን መወያየት አለብን። የተለያዩ ግለሰቦችና አንዳንድ ድርጅቶች ይህንን አገዛዝ በኃይል ካልሆነ በስተቀር ማንበርከክ አይቻልም ብለው ከተነሱት ጥቂት ኃይሎች በስተቀር እኔም ሆነ አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብና ታጋይ በሰላም መንገድ ከመታገል ሌላ አማራጭ እንደሌለ አምነንበታል። አንደኛውና ፍቱን መሳሪያ

***ምሁራዊ ትግል ማካሄድ ነው። በተወሰነ ሃሳብ ዙሪያ መሰብሰብና በተከታታይ መጽሄትም ሆነ ጋዜጣ በማውጣት የሰፊውን ህዝብ ንቃተ-ህሊና ማዳበር ፍቱን የሰላም ትግል መሳሪያ ነው። የተቀነባበረ የጋዜጠኝነት ስራ መስራት ጊዜያዊና አስፈላጊ ነው። ጽሁፎች አገር ቤት ገብተው እንዲነበቡና ሰፊው ህዝብ እንዲረዳቸው ማድረግ ያስፈልጋል። ሌሎች የዜና ማሰራጫዎች እንደ ፓል ቶክና ሬዲዮ ጣቢያዎች የመሳሰሉት ከንትርክና ከተራ ዜና አልፈው ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች እየተዘጋጀባቸው የሚቀርቡበት መንገድ መፈለግ አለበት። ምሁራዊ ጽሁፍና ዜናዎች ብቻቸውን የትግል መሳሪያ ሊሆኑ አይችሉም። ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግና የቤት ውስጥ አድማዎች ሊታለፉ የማይችሉ ሰላማዊ የመታገያ መንገዶች ናቸው። ከዚህ ውጭ ሊታሰቡ የሚችሉ መዐት መንገዶች አሉ። ዋናው ነገር እነዚህን እንዴት እናቀነባብር ነው። እንዴት ፋይናንስ እናድርግ ነው። በሌላ ወገን የዓለም ኮሚኒቲውን እናሳምናለን እየተባለ እዚህና እዚያ የሚደረገው ሩጫ ትግላችንና ሃሳባችንን የሚበታትን ነው ። የዓለም ኮሚኒቲው የሚባለው ማንኛውም ፓርቲ ይሁን በጣም አጭበርባሪ ነው። ደግሞም ለብሄራዊ ነፃነት የሚደረገው ትግል በልምምጥና አንገትን በመድፋት ላይ የተመሰረተ ሊሆን አይችልም። የአውሮፓንና የአሜሪካንን ታሪክ ለተመለከተ ትልልቅ አገር የተመሰረተው በቆራጥነትና ሰፋና ጠለቅ ባለ ምሁራዊ እንቅስቃሴ አማካይነት ብቻ ነው። ለዚህም የታሪክ ማህደሮችን ማገላበጥ ያሰፈልጋል። ይህ ግንዛቤ ውስጥ ሲገባ ብቻ አንድ እርምጃ ወደ ፊት ተራመድን ማለት ነው። ተንኮልንና መጠላለፍን እንዲሁም ለራሴ ብቻ የሚለውን ስግብግብ አስተሳሰብ ትተን ለአንድ ዓላማ ከተነሳን የድሉ ቀን ሊዘገይ አይችልም። ለአንድ አገር ህዝብ ዕድገት ውስጣዊ ፍላጎትና የህሊና ጽናት እጅግ አስፈላጊ መሆናቸውን ተገንዝበን ያቹን አገር ከጥፋት የማዳን ታሪካዊ ኃላፊነት አለብን።***

**ፈቃዱ በቀለ**

***<u>ማሳሰቢያ፡</u>*** ***የሁለት ሺው ዐመት ጠመዝማዛ ጉዞ ! የሚቀጥለውስ ምን ዐይነት ጉዞ ! የፍራንክፈርቱ የክሌተ አመዓት አከባበር በሚለው ከአንድ ወር ተኩል በፊት በተለያዩ ድህረ ገጾች ላይ በወጣው ጽሁፌ ላይ በቀኑ ተጋብዘው ንግግር ካደረጉት የዶቹ ቬለው ሰራተኛ አቶ ተክሌ የኋላ ይገኙበታል። የኝህን ምሁር ስም በስህተት ክፍሌ በሚል አውጥቼዋለሁ። ይቅርታ እየጠየቅሁ አቶ ተክሌ የኋላ ተብሎ እንዲነበብልኝ አሳስባለሁ።***